# የቻንስለሩ የወላጅ ካቢኔ አጠቃላይ ገጽታ

**አጠቃላይ ገጽታ**

የቻንስለሩ የወላጅ ካቢኔ (Parent Cabinet) ለወላጅ መሪዎች፣ ትምህርት ቤቶች ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩ ሥልት አቀፍ ፖሊሲዎች ዙሪያ ቻንስለሩን ቀጥታ እንደሚያ ስገነዝብ አካል ሆነው ያገለግላሉ። አባላቱም በዲሲፒኤስ ቢያንስ አንድ ልጅ ያላቸው ወላጆች (ገና ለወደፊቱም የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ወላጆች ሊሆኑ የሚችሉትንም ለመቀበል ፈቃደኞች ነን። እነዚህም የልዩነት ስፋት ያለውን በርካታ የዲሲፒኤስ ማኅበረሰብን የሚያንጸባርቁ ይሆናሉ። ስብሰባዎችም ቻንስለሩን፡ አባላትን እና ዋና ዋና የዲሲፒኤስ መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን ይይዛል።

**የወላጅ ካቢኔቱ አወቃቀር እንዴት ነው?**

የወላጅ ካቢኔቱ፣ በበጎ ፍቃደኝነት የሚያገለግሉ ከ 16-24 ወላጆችን የሚያቅፍ ይሆናል።

**በወላጅ ካቢኔት ውስጥ ለማገልገል ፍላጎት ላላቸው ወላጆች የአቀባበሉ ሂደት እንዴት ነው?**

ወላጆች ለ3 ጥያቄዎች መልሶችን በመስጠት የጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው። በሚከተሉት መንገዶች አማካይነትም ማመልከት ይችላሉ።

- *(ተመራጩ መንገድ) በ* http://bit.ly/ChancellorParentCabinet *ኦን ላይን ላይ ማመልከት*
- በ Jennifer.skates@dc.gov ኢሜይል አማካይነት ለ ጀኒፈር
- በ 202.442.5026 ፋክስ አማካይነት
- በዩኤስ ፖስታ አገልግሎት አማካይነት ለ DCPS; 1200 First Street, NE; 12th Floor, WDC 20002; *(በ 2/8/14 ፖስታ ቤት ገቢ ለመሆኑ የፖስታ ቤት ማኅተም ያረፈበት) ሆኖ* C/O Chancellor's Parent Cabinet በሚል ማመልከት።

የዲሲፒኤስ ወላጆች፣ ርእሠ መምህራን እና መምህራን በተጨማሪ ማመልከቻ በመሙላት እና ለ Jennifer.skates@dc.gov. ኢሚይል በማድረግ ለወላጅ ካቢኔው ወላጆችን መምረጥ ይችላሉ። ማመልከቻዎች እና ምርጫዎች <u>ሁሉ</u> ማክሰኞ፣ የካቲት (February) 11, 2014 በ 11:59 ፒኤም ላይ ገቢ መሆን አለባቸው። የተ መረጡ ወላጆች በዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት በአካል ቀረበው እንዲያመለከቱ ይፈቀዳል። በአካል ቀርበው ለአመለከቱ ማመልከቻዎች የሚደረጉ ቃለ መጠይቆች ቀደም ብሎ ጊዜ የሚያዝላቸው ሲሆን (እግር እንደጣለ መምጣት) አይፈቀድም።

**የወላጅ ካቢኔት አባላት ለአገልግሎት የሚመረጡት እንዴት ነው?**

ሰፊ ውክልና አቀፍ ያለው መሆኑን ዕውን ለማድርግ፣ ማመልከቻዎች እና ተመራጮች፣ ከተማይቱን በሞላ በስፋት የሚወክሉ መሆንን ለማረጋጋጥ የመኖሪያ ቦታን፣ የልጁን የክፍል ደረጃን፣ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብን፣ የዝንባሌ መስኮችን እና ገጠመኞችን ጨምሮ በበርካታ ነጥቦች አኳያ ይገመገማል። እኛ በተለይ ፍላጎታችን ያደረው ከወላጅ ካቢኔ ስብሰባዎች የተቃረሙ አስተያየቶችን ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመጋራት ፈቃደኛ በሆኑ ወላጆች ላይ ነው።

**የወላጅ ካቢኔት ስብሰባዎች የሚካሄዱት መቼ ነው?**

የወላጅ ካቢኔ ስብሰባዎች በየወሩ 2ተኛው ማክሰኞ በሚውልበት ቀን ለአንድ ድፍን ዓመት እንዲከበር በማድረግ፣ መጋቢት (March) 19, 2014 ከ 6:00 ፒኤም – 7:30 ፒኤም ድረስ ሥራ ላይ የሚውልበት ቀን በማድረግ ይከበራል። ስብሰባዎቹም በ 1200 First Street, NE ላይ ይካሄዳሉ።

**ከወላጅ ካቢኔው ምን ይጠበቃል?**

የወላጅ ካቢኔ አባላት የሚከተሉትን እንዲያካሂዱ ይጠበቃሉ፤

- እንዲካሄዱ ጊዜ በተያዘላቸው ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ መሳተፍ። .
- እንደ አስፈላጊነቱ ለእያንዳንዱ ስብሰባ ዝግጅት ማድረግ።
- ትብብር በተሞላበት ሁኔታ ከእርስ በእርስ እና ከዲሲፒኤስ መምህራን እና ሠራተኞች ጋር አብሮ መሥራት።
- ግልጽነት፣ ገንቢነት፣ እና አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ሀሳቦችን እና አስተያየቶችን መግለጽ።
- ከአቻዎች ጋር እና ስለ እነሱም ሆኖ መረጃዎችን መለዋወጥ።